# ከእውነተኛው አምልኮ ጎን ቁም (ክፍል 2)

JW.ORG

ይህ ትምህርት የተመሠረተው ትክክለኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ምንድን ነው? በተባለው መጽሐፍ ምዕራፍ 16 ላይ ሲሆን መጽሐፉ jw.org/am ላይ ይገኛል።

**ዓላማው፦ ምን ብለህ እንደምታምንና እንዲህ ያለ እምነት ልታዳብር የቻልክበትን ምክንያት ፈትሽህ ለማወቅ እንዲሁም መጽሐፍ ቅዱስ ምን እንደሚያስተምርና እምነትህን ለሌሎች ማስረዳት የምትችለው እንዴት እንደሆነ ለመመርመር።**



## እውነተኛ ክርስቲያኖች ስለ እምነታቸው ለሌሎች መናገር አለባቸው?

### 1 እምነትህን ፈትሽ

አንዳንድ ሰዎች አዎ የሚል መልስ የሚሰጡት ለምንድን ነው?

______________________________________________

______________________________________________

አንዳንድ ሰዎች አይ የሚል መልስ የሚሰጡት ለምንድን ነው?

______________________________________________

______________________________________________

አንተስ ምን ብለህ ታምናለህ?

______________________________________________

እንዲህ ብለህ እንድታምን ያደረገህ ምንድን ነው?

______________________________________________

______________________________________________



www.jw.org/am © 2017 Watch Tower Bible and Tract Society of Pennsylvania

## 2 መጽሐፍ ቅዱስ ምን እንደሚያስተምር መርምር

**እውነተኛ ክርስቲያኖች ስለ ሃይማኖታዊ ጉዳዮች ከሌሎች ጋር ከመከራከር ይቆጠባሉ።**

*(የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት የተባለውን መጽሐፍ ምዕራፍ 16 ከአንቀጽ 13-17 ተመልከት።)*

### ቆላስይስ 4:6ን አንብብ።

ይህ ጥቅስ ስለ እምነታችን ለሌሎች ስንናገር ዘዴኞች መሆን እንዳለብን የሚያመለክተው እንዴት ነው?

___

___

___

### ማቴዎስ 7:12ን አንብብ።

ሌሎች ሰዎች የምናምንበትን ነገር ባይቀበሉም እንኳ አክብሮት ልናሳያቸው የሚገባው ለምንድን ነው?

___

___

___



**ከሰዎች ጋር የኳስ ቅብብሎሽ ስትጫወት፣ ኳሱን አብሮህ የሚጫወተው ሰው በቀላሉ እንዲይዘው በሚያደርግ መልኩ ለመወርወር ጥረት ማድረግህ አይቀርም። በተመሳሳይም ለሌሎች ስለ እምነታችን ስናብራራ ሰዎች አመለካከታችንን እንዲረዱት በሚያደርግ መንገድ በዘዴ ማብራራት ይኖርብናል**


www.jw.org/am © 2017 Watch Tower Bible and Tract Society of Pennsylvania

**እውነተኛ ክርስቲያኖች ከእምነት ባልንጀሮቻቸው ጋር በመሰብሰብ ስለ እነሱ ይበልጥ ማወቅ ለሚፈልጉ ሰዎች እምነታቸውን ማስረዳት የሚችሉት እንዴት እንደሆነ ይማራሉ።**

*(የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት የተባለውን መጽሐፍ ምዕራፍ 16 ከአንቀጽ 18-19 ተመልከት።)*

## መዝሙር 22:22ን፣ ሮም 1:12ን እና ዕብራውያን 10:24, 25ን አንብብ።

ከእምነት ባልንጀሮቻችን ጋር ለአምልኮ መሰብሰባችን ምን ጥቅም ያስገኝልናል?

## ሚልክያስ 3:10ን አንብብ።

ከእውነተኛው አምልኮ ጎን ከቆምን ምን ጥቅም እናገኛለን?

*አንተስ ስለ እምነትህ ለማን መናገር ትችላለህ? ይህንን በዘዴ ማድረግ የምትችለውስ እንዴት ነው?*



www.jw.org/am © 2017 Watch Tower Bible and Tract Society of Pennsylvania

## 3 እምነትህን ለሌሎች አስረዳ

አንድ ሰው እንዲህ ቢልህ . . .

**የይሖዋ ምሥክሮች ሌሎች የእነሱን እምነት እንዲቀበሉ ያስገድዳሉ።**

እንዲህ ብለህ መመለስ ትችላለህ . . .

**እርግጥ ስለ እምነታችን ማወቅ ለሚፈልጉ ሰዎች የምናምንባቸውን ነገሮች ማስረዳት ያስደስተናል። ሆኖም እምነቱን እንዲቀይር ማንንም ሰው አንጫንም፤ ምክንያቱም . . .**

____________________

____________________

ለግለሰቡ የትኛውን ጥቅስ ልታሳየው ትችላለህ?

____________________

የግለሰቡን አመለካከት ግምት ውስጥ በማስገባት ይህን ጥቅስ ልታብራራ የምትችለው እንዴት ነው?

____________________

አንድ ሰው እንዲህ ቢልህ . . .

**ሃይማኖት የግል ጉዳይ ነው፤ ስለዚህ ከሌሎች ሰዎች ጋር ስለ ሃይማኖት መነጋገር ተገቢ አይደለም።**

እንዲህ ብለህ መመለስ ትችላለህ . . .

**በዛሬው ጊዜ ያሉ ብዙ ሰዎች እንደዚያ ዓይነት አመለካከት አላቸው። መጽሐፍ ቅዱስ ግን ስለ እምነታችን ከሌሎች ጋር እንድንነጋገር ያበረታታናል፤ ምክንያቱም . . .**

____________________

____________________

ለግለሰቡ የትኛውን ጥቅስ ልታሳየው ትችላለህ?

____________________

የግለሰቡን አመለካከት ግምት ውስጥ በማስገባት ይህን ጥቅስ ልታብራራ የምትችለው እንዴት ነው?

____________________



www.jw.org/am © 2017 Watch Tower Bible and Tract Society of Pennsylvania